EFDA
የኢትዮጵያ ምግብና መድኃኒት ባለሥልጣን
ETHIOPIAN FOOD & DRUG AUTHORITY

ከኢትዮጵያ የምግብና መድኃኒት ባለሥልጣን
ጋር በመተባበር በየ15 ቀኑ የሚታተም

# ስለ መድኃኒት ደህንነት ቁጥጥር ምን ያውቃሉ?

## የመድኃኒት ደህንነት ቁጥጥር ማለት ምን ማለት ነው?

የመድኃኒት ደህንነት ቁጥጥር ማለት በገበያ ላይ ስላሉ መድኃኒቶች ደህንነት መረጃ የሚሰበሰብበት፣ የሚተነተንበት እና እንደ አስፈላጊነቱ ለማስተማሪያነት እና ለመከላከል የምንጠቀምበት ስርዓት ነው።

## የመድኃኒት ደህንነት ቁጥጥር ለምን ያስፈልጋል?

መድኃኒቶች ተጠንተው ጥቅም ላይ እንዲውሉ የገበያ ፈቃድ በሚያገኙበት ወቅት ስለ መድኃኒቱ የሚኖሩ የደህንነት መረጃዎች ውስን በመሆናቸውና መድኃኒቶች በስፋት ጥቅም ላይ በሚውሉበት ወቅት ቀጣይነት ያለው ክትትል ማድረግ ስለሚያስፈልግ ነው። በተጨማሪም አንድ አንድ የመድኃኒት የጎንዮሽ ጉዳቶች በተለይም አስከፊ የሆኑ በጥቂት ቁጥር እና በጊዜ ርዝመት የሚከሰቱ ችግሮችን መለየት እና ማወቅ የሚቻለው መድኃኒቱ በስፋት እና ረዘም ላለ ጊዜ ጥቅም ላይ ሲውል በመሆኑ የመድኃኒት ደህንነት ቁጥጥር ያስፈልጋል።

## የመድኃኒት ደህንነት ቁጥጥር በማን ይከናወናል?

የመድኃኒት ደህንነት ቁጥጥር እንደ ሀገር ኃላፊነትና ስልጣን የተሰጠው በአዋጅ ቁጥር 1112/2011 ለኢትዮጵያ ምግብና መድኃኒት ባለስልጣን ሲሆን፤ ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ይህንን ተግባር ለማከናወን ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት ይሰራል። ከባለድርሻ አካለት ውስጥ በጤና ተቋማት ውስጥ የሚሰሩ የጤና ባለሙያዎችና ሕብረተሰቡ (መድኃኒት ተጠቃሚው) ጉልህ ሚና አላቸው።

## የመድኃኒት ደህንነት ቁጥጥር እንዴት ይከናወናል?

የኢትዮጵያ ምግብና መድኃኒት ባለስልጣን በአዋጅ በተሰጠው ስልጣንና ኃላፊነት መሰረት ገበያ ላይ የሚውሉ መድኃኒቶችን ደህንነት፣ ፈዋሽነትና ጥራት ለማረጋገጥ የተለያዩ የአሰራር ስርዓቶችን ዘርግቷል። በዚህም መሰረት የመድኃኒት ደህንነት ቁጥጥርን ለማረጋገጥ የተለያዩ የመድኃኒት የጎንዮሽ ክስተት ሪፖርት ማድረጊያ ቅጾችን በማዘጋጀትና ለጤና ባለሙያው በማሰራጨት፣ ለጤና ባለሙያዎች የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎችን በመስጠት፣ የአሰራር መመሪያዎችን በማዘጋጀት ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት በማዳረስ እና ተፈፃሚነታቸውንም ክትትል የማድረግ ተግባራትን እያከናወነ ይገኛል።

## ከማን ምን ይጠበቃል?

## ከሕብረተሰቡ/መድኃኒት ተጠቃሚው

ማንኛውም ሰው መድኃኒት በሚታዘዝለት ወቅት ስለ መድኃኒቱ አስፈላጊውን መረጃ ከባለሙያዎች በድንብ መጠየቅ እና መረዳት አለበት። በተጨማሪም፣ መድኃኒት በሚጠቀምበት ወቅት ማንኛውም አይነት የጎንዮሽ ክስተት ሲያጋጥመው መድኃኒቱን ያዘዘለት ባለሙያ ጋር በመሄድ ችግሩን ማሳወቅና የሚሰጠውን ምክር እና ሕክምና በአግባቡ መተግበር አለበት።

## ከጤና ባለሙያው

የጤና ባለሙያዎች በእለት ተእለት ተግባራቸው ለታካሚዎች በአንድም በሌላም መንግድ ሕክምና ሲሰጡ የሚውሉ በመሆናቸው፤ የመድኃኒት አወሳሰድ ስርዓት እና ከመድኃኒት ጋር ተያይዘው ስለሚያጋጥሙ የጎንዮሽ ክስተቶች ለታካሚዎች ቀድመው የማሳወቅ እና ችግሮች ሲከሰቱም አስፈላጊውን ሕክምና የመስጠት ኃላፊነት አለባቸው። በተጨማሪም፣ የጎንዮሽ ክስተት ሪፖርቶችን ወደ ምግብና መድኃኒት ቁጥጥር ባለስልጣን ሪፖርት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።

## ከተቆጣጣሪ አካላት

በየደረጃው የሚገኙ የተቆጣጣሪ አካላት ስለመድኃኒት የጎንዮሽ ክስተት የማሳወቅ፣ የጤና ባለሙያውን ስለ መድኃኒት የጎንዮሽ ክስተቶች ላይ ማሰልጠን እና የክትትል ስርዓቱን ለማከናውን የሚያስፈልጉ ግብዓቶችን ማለትም፡ መመሪያ፣ ጋይድላይን፣ ሪፖርት ማድረጊያ ቅጾችን ለጤና ተቋማት የማዳረስ እና የጎንዮሽ ክስተቶች ሪፖርቶችን የመሰብሰብ ኃላፊነት አለባቸው። በተጨማሪም፣ ከፍተኛ ጉዳት ያስከትል የጎንዮሽ ክስተት ሪፖርት በሚቀበሉበት ወቅት አስቸኳይ የማጣራት ስራን በማከናወን ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ግብረመልስ መስጠት ይጠበቅባቸዋል።

Tel : +251-11-552-41-22
+251-11-552-41-22
P.o.box. 5681
Free call. 8482

http://www.fmhaca.gov.et/contact/
E-mail contactefda@efda.gov.et
Telegram channel link
https://t.me/ethiopianfoodanddrugauthority/

በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ